ክንፈ ሚካዔል
ሀምሌ 11፣ 2000 ዓ/ም

ከጥንት ገጣሚዎች ቁጥር 2*

አ/ኪ/ወ/ክፍሌ

ከሁልት ዛፍ ለወደቀው
ያላገር ቋንቋ ማነው አንሺው
ስሟ ጣይቱ የግዕዝ ቋንቋ
አማርኛዋ ኮከብ ጨርቃ።
ፊደሏ ብርሀን ዘእመብርሀን
ሰባት ቁልጭልጭ የግዜር በግ ዐይን።
ግዕዝ ግዕዙ ወርቅ ቀለም
ባለ 6 ዐጽቅ ጎንደ ተቋም
ስድስቱም ዐጽቅ ግራና ቀኙ
ከሱራፌል ክንፍ የተገናኙ።
ፍሬ ነገሩ ግዕዝ ሳይጸድቅ
ፍሬ አያፈራም አማርኛ ዐጽቅ።

ዐጽቅ፦ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉት ፊደላት ናቸው

======================

ሠዓሊ አገኘሁ እንግዳ
ሐምሌ 1927 ዓ/ም

ኢትዮጵያ እናቴ አንቺን ደስ ይበልሽ ጠላትሽ ይዘን፣
ድንበርሽ አይጠብም ልቾችሽ ሳለን፥
ምንም ጦር ቢከበን ዙርያ ገባውን፣
ወደ ኋላም አንቀር ልማድም የለን::

=====================================

ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ
አ. አ. ነሐሴ 18 ቀን 1927 ዓ/ም

የወንድ ልጅ ኩራት  ስለ ሀገር መሞት
ስማኝ ያገሬ ልጅ ልንገርህ ጥቅም፣
ካገርህ ልጅ ጋራ ተፋቀር በጣም፣
የሰው አገር ወዳጅ ብዙ አያዘልቅም#
አገሬን አገሬን እንበል ሁላችን፣
ግፉ በዝቷል እና በየወሰናችን፤

====================

ሀብተ ማሪያም

መቼ አሁን ሆነና ይህማ ጠባችን፣
የቆየ አይደለም ወይ ቀድሞ ካባታችን፤
ቆርጠንም አንሰጥ እኛስ ከርስታችን፣
እንማከራለን እንደ ልማዳችን፤
የዘር ባለጋራ ምን ቢለማመኑት፣
አይተውም ማመሙን ደም ካልፈሰሰለት፣
ወሰን ገፊ አይለቅም ምሱ ካልሆነለት፤
===========================

ወይዘሮ የሺመቤት ገነሜ

በተባበረ# ሀይል አንድነት ሆናችሁ፣
እንግዲህ ጠንክሩ እርስ በራሳችሁ፣
ለኢትዮጵያ ስትሉ# ለደግ እናታችሁ፣
ጠላቷን አጥፉላት እየተራዳችሁ፤
==============================

- ቁጥር 1 የታላቁ ገጣሚ የመንግስቱ ለማ ነው። ከሱ እንዲቀጥል በማሰብ ነው ቁጥር 2 ያልኩት

# እኔ የጨመርኩት ነው

ሀሰን አማኑ

መቼ ሞተና መቼ ተረሳ፣
መቅደላ ያለው የቋራው ካሳ፤

ወዳጁም ሳቀ ጠላቱም ከሳ፣
ተንቀሳቀሰ ዳኛው ተነሳ፣
አራቱ አህጉር ለሱ እጅ ነሳ፤

የትግሬ መሬት ይብላኝልህ፣
ቀሩብህ ባንተ እነገበየሁ እነበሻህ

አሻግሮ ገዳይ ዲብ አንተርሶ
የዳኛው አሽከር ባልቻ አባ ነፍሶ
=============================

ከንቲባ ገብሩ ደስታ

አ.አ. 1915 አ/ም

ካፉፉ ላይ ሆኖ የሚጣራው ማነው፣
የኛ ሰው ይሆናል ወይ በለው ወይ በለው፤
ለኔስ ትዝ የሚለኝ የናፈቀው ልቤን፣
ኢትዮጵያ ራሷን የምትችልበት ዘመን፤
አንበላም ወይ እኛ በጃችን ሰርተን፣
ለምን አንሳቀቅ የሰው እጅ አይተን፤

===============================

*ሰለሞን ደሬሳ*
*ልጅነት፣ 1963*
*ድንቄም ዕውቀት*

የተመራመረው ሞዝቮልድ ነው ጠረጴዛው
ፔዠ ነው ፈረሱ
ፈረሱ ፔዠ ነው
ሳይቸከን ሞዝቮልድ ፔዠን ትተን
በቁም ነገር እስቲ ሌላ ዘፈን።
እሰይ እሰይ እሺ! ባዩ
እሰይ እሰይ ቶምቦል ባዩ
እንዲያ እንዲያ አባባዩ
እሰይ እሰይ ሲያዩ ባላዩ
እሰይ እሰይ ባላዩ ሲያዩ
አዋቂ ይባላሉ
ጨክኖ ባታለሉ
ጥረት ባስተያዩ
ድንቄም ዕውቀት
መታጠን ለማያቁት
ደርሶ ቅሌት
=======================

ሀይሉ ገ/ዮሐንስ
ዛር ነው በሽታዋ፣ 1991

ግን ዋ ያ ቅኔአችን ካልኩለስ በነበር
ዋ ያ ብሉይ ያ ሐዲስ አልጀብራ በነበር
ዋ ያ መሳጭ ዜማችን ፊዚክሲም በነበር
እንዲያ ያርጋጅ እንጎጅ አድናቂ አጨብጨቢ
ሆነን ባንቀር።
ሆኖማ በነበር ቅኔአችን ካልኩለስ

ማነው እኛን ቀድሞ አፓሎ እሚተኩስ
ሆኖማ በነበር ዜማችን አልጀብራ
ማነው ከኛ በፊት ስለሰማይ ምስጢር ቀድሞ የሚያውራ
ሆናማ በነበር ብሉይ ሀዲሳችን ድጓው ጾመ ድጓው ፊዚክስ ኬሚስትሪ
እንዴት ያለው ይሆን ከኛ በፊት ቀድሞ ሮኬት ወርዋሪ ሳተላይት አብራሪ
ጥንተ መሰረቱ እንዲያ እንዳልነበር
በድህረ አለሙ ጉባኤያት ሁሉ የኛ ውብ ነበር
ማንኛውም ነገር።
==========================================

<u>ሰይፉ መታፈሪያ</u>
    ነገር፣ 1981
ትንሽ የነገር ድንጋይ
ድቡልቡል
ሙዳ ስጋ ትመስል
ሄዳ ሄዳ ቅርቅር
ከጉሮሮና ጉሮሮ መሀል
ስሜት የማሳመም ስራ
ውስጠት ቡርቡራ
ከወደ ልብ ነው የመጣችው ሽቅብ
እና ሄዳ ገባች ከጭንቅላት
መቼ እንደምትወጣ እንጃላት
========================

<u>ነጋሽ ገ/ማሪያም</u>
በድዱ ይስቃል

ደጉ ጊዜ አለፈ የዛሬው ይቅር
ትቻለሁ መጓጓት ለጥሩ ነገር
የትዬ ሌሌ ነው የሽመታው ጣጣ
ሀምሳ ብር ተሽርፋ ለስንቱ ልትመጣ።
ምኑን ከምን ላርገው እናንተ ፍረዱ
ስጋ ቂቤው ቀርቷል ጥሬው መወደዱ
ብለው አማረሩ በመንግስት ፈረዱ።
==========================

<u>ከበደ ሚካዔል</u>
 የቅኔ ውበት፣ 1961

ሊፈጠር ከሚችል ከውጭ አደጋ
የውስጥ እንቅፋት ነው በጣም የሚያሰጋ

ውስጡ ካልበረታ ካላገኘ ሀብረት
እንደምን ይቻላል የውጭውን መመከት።
መንታ መንገድ ናቸው መጥፋት እና መዳን
ምንም መሪ የለን ለዚን የሚረዳን።
==================================

<u>አፈወርቅ ገ/እየሱስ</u>
የዳግማዊ ሚኒሊክ ወቀሳ፣ 1909 ዓ/ም አስመራ

እረ ስማ ስማ የኢትዮጵያ መኳንንት
ገደል ያገባሀል ባዕድ ምክር መስማት
በውስጥ መርዙን ቀብሮ ላይ ላዩን ወተት
አድርጎ ያቀርባል እንዲወደድለት።
===================================

<u>አቤ ጉበኛ</u>
አንድ ለናቱ፣ 1961

ምነው አገሬ ሆይ እስቲ ተጠየቂ
ሰውን ማጥፋት እንጂ ሰው ማብቀል አታውቂ
ሀገሬ ሀገሬ ሀገሬ ሀግሬ
ባንቺ ተወልጄ ባንቺ ላይም ኑሬ
ባንቺ ላይ ነግጄ ባንቺ ላይ ቆፍሬ
ስላንቺ ተኩሼ ስላንቺ ወርውሬ
ባንቺ ላይ ደህይቼ ባንቺ ላይ ከብሬ
ደግሞ ላገኝ ክፉ ላንቺ ላንቺ ጥሬ።
======================================

<u>ግርማ ታደሰ</u>
ተናገር አንተ ሀውልት

ተናገር አንተ ሀውልት አክሱም ላይ ያለኸው
ለሶስት ሺህ ዘመን ስንት ጉድ ያየኸው።
====================================

<u>ጎርፉ ገ/መድህን</u>
አጤ ቴዌድሮስ

የቋራው አንበሳ ካሳ
በመቶ አመቱ ቢያገሳ
ስንቱን ቀሰቀሰውሳ
=========================

ፈቃደ አዘዘ
ጩኸት፣ 1982

እኔ አውቃለሁ

ባህር ማዶ ሆነን በናፍቆት ሰቀቀን
ከሀገር ቤት ሆነን በፍርሀት ተሰልበን
መች ተባበርንና
የየግል ሯጮች
የየጎጥ ባንዲሮች
ተምሮ ጀብደኞች
የስድብ ታንከኞች።

መች ህበረት መሰርተን
የቀዬ መንግስቶች
መች ባሳብ ተሟገተን
መቼ ተቻችለን በዕቀት በልጽገን
በወንዜ ወንዜ ልጅ በተማሪ ቤቴ
ፅዋ ተዘካክረን ጥይት ተረጫጭተን
መቼ በህግ ሰርተን
=================================

ቴዎድሮስ አበበ
ህልም፣ 2005

ምን ትመኛለህ ብትሉኝ
መመኜቴ ካልከፋ
አገር በቀል ስርዐት
በኢትዮጵያ ልክ የተሰፋ
ለባህሏ የሚስማማ
የብስ ውሀዋን የሚያለማ
ዕምነቷን የሚያዳብር
ታሪክ ቅርሷን የሚያዳብር
ማህበራዊ ትሥስሯን
የፈሪሀ እግዚአብሔር ውርሷን
የሚያፀና
ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና ነው ለማየት የምመኘው
የማልመው።
"ማርክሲዝ፣፣
"ኮሚኒዝም"
"ፌዴራሊዝም"

እንደ ሸቀጥ ያራከሳት የባዕድ ፓለቲካ
በኢትዮጵያኢዝም እንዲተካ
ነው ለማየት የምመኘው
የማልመው::
====================================

<u>ገ/ክርስቶስ ደስታ</u>
ፍቅር ጥላ ሲጥል

በገና ቢቀኙ
ሽክላ ቢያዘፍኑ
ክራር ቢጫወቱ
ለሚወዱት ምነው።
ሙዚቃ ቢመቱ
ቢቀኙ
ቢያዜሙ
ቃል ቢደረድሩ
ጌት ውበት ቢፈጭሩ
ቤት ንብረት ቢሰሩ
አበባ ቢልኩ
ደብዳቤ ቢልኩ
ለሚወዱት ምነው?
ሲናፍቁ
አገር ቢያቋርጡ
ቢሄዱ ቢርቁ
አመት ቢጠብቁ
ዘመን ቢጠብቁ
ለሚወዱት ምነው?
================================

<u>ፀጋዬ ገ/መድህን</u>
ሀሁ ወይም ፐፑ
አበባ ወይ እሳት
አስራ ሰባት አመት በደገሰው ሰርግ
ጓድ ኢሰፓ ደርግ
አማክሎ ገባበት ወያኔ ኢህአዴግ
ምነው እኮ ፍቅር ነሳን
ምነው እኮ ሰላም ነሳን
ያንድ እናት ልጅ ቢከፋፋም
ከምድር ገፅ እስኪጠራረግ ፋሺስትነት አይገነባም

እናቶች አባቶች

አህቶች ወንድሞች
ተበላን በምሁር ጆቦች
የልባችን ቋት ጨለመ
ብልጭታው ተረመረመ።

ባንድ ጆራፍ ለተገረፍን
ባንድ እርግማን ለተኮነንን
እኛው ነን የኛ መድህኒት
ከኛ እንጂ ከውጪ አይመጣም
የነገ ተስፋችን መክሊት።
=====================================

*<u>መንሰቱ ለማ</u>*
*መርፌ፣ 1967*
*ያገሬ ባላገር "የተማረ"ን ሰው*
*ካውሮፓ ሲመለስ ሊመረምረው*
*"መርፌ ትሰራለሕ" ይለዋል እያሉ*
*ያጫውቱኝ ነበር ሟቹ ዶ/ር ክንፈ*
*በፈረንሳይ አገር እድሜአቸው ያለፈ።*
*ፊደል ያልቆጠረ የዋህ ያመርና*
*ደርሶብኛል አሉኝ "እንዲህ ያለ ፈተና"*
*መልሱ የማይታወቅ ቢጠና ቢጠና*
*ባላገር እና እኔ እወይ መከራ እዳ*
*ፊት ለፊት ተጋጨን ድንገት "ሰንነዳ"*
*ሸፍረሌቴን እኔ እሱ አህያውን*
*ምንድን ሊጠይቀኝ ምን ሊለኝ ይሆን*
*ከእግር እስከ ራሴ ቢመለከተኝ*
*መረፌ ትሰራለህ የመጣ መሰሎኝ*
*ተመኘሁ በልቤ ቢቀረጥ ምላሱ*
*በጥፋት ያለቀ ድሪቶ ነው ልብሱ*
=======================

ዋቤ መጻህፍት
1. ዝክረ ነተር፣ ነጻነት ማተሚያ ቤት፣ 1942 ዓ/ም፣ ማህተም ሥላሴ ወ/መስቀል (ብላቴን ጌታ)
2. ንባባ ወትርጓሜ ዘቅኔአት አዕማደ ሚስጥራት፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት ቅጽ 6 ቁ.2፣ 1960 ዓ/ም መ/ር ይኼይስ ወርቄ
3. ብሌን ቁጥር 2፣ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር
4. ሀሁ ወይም ፐፑ አበባ ወይ እሳት፣ ዩሪካ፣ (ዓ/ም የለውም) ፀጋዬ ገ/መድህን (ብላቴን ጌታ)
5. ያማርኛ ሰዋሰው መሪ፣ 1915 ተፈሪ ማተሚያ ቤት፣ ገብሩ ደስት

6. የቅኔ ውበት፣ ሜጋ፣ 1995 ከበደ ሚካዔል
7. መጽሐፈ ሰዋሰው ወግዕዝ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ አርቲስቲክ ማትሚያ ቤት፣ አለቃ ኪ/ወ/ክፍሌ